# ሊቃውንቶቻችን

የጋስጫው አባ ጊዮርጊስ

ሊቅ በሚያሰኙ በትምህርት ደረጃቸው በምርምር ስለታቸው በሥነ ጽሑፍ አቀራረባቸው ፤ እንዲሁም በብቃትና በመንፈስ ቅዱሳዊ ሀብት በተቃኘው ሰብአዊ ሁኔታቸው የታወቁ የኢትዮጵያዊው የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ታሪክ ከብዙው በጥቂቱ እንሆ በዚህ ዓምድ ላይ እናቀርባለን ።



ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

## ሐረገ ትውልድና ዘመነ ልደት

የትውልድ አገራቸው ትግራይ የሆነው የአባ ጊዮርጊስ አባታቸው ሕዝበ ጽዮን ፤ እናታቸው የወለቃ ቦረና ተወላጅ እምነ ጽዮን ይባላሉ ።

ባልና ሚስት የነበሩት ሕዝበ ጽዮንና እምነጽዮን ለረጅም ዘመን በመካንነት ከኖሩ በኋላ የመውለድን በረከት እንዲያገኙ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል እናት እንደነቢይት ሐና ወደፈጣሪያቸው አመለከቱ አባ ጊዮርጊስ በ1357 ዓ.ም. በጥቅምት 3 ቀን ተፀንሰው በዚሁ ዓመተ ምሕረት በሐምሌ 7 ቀን መወለዳቸውን ታሪካቸው ይረጋግጣል ።

## የትምህርት ይዞታቸው

የታሪካቸውን ሒደት በማስመልከት ከታሪክ ተከታታዮች እንደተገኘው ወላጆች አባታቸው አባ ጊዮርጊስን አባ ሠረቀ ብርሃን የተባሉ የሐይቅ መምህር እንዲያስተምሩላቸው በአደራ ሰጥተዋቸው ለሰባት ዓመት ተምረዋል ። ከዚህም በቀር የያሬዳዊ ዜማ ጥናታቸው ሙሉ በሙሉ ተቃንቶላቸው ሊቅ የሚያሰኛቸውን ከፍተኛ ስም ለመውረስ ችለዋል ተብሎ ይተረካል ዝርዝር ሁኔታው በታሪክ መጻሕፍት ተመዝግቧል ።

## የሥነ ጽሑፍ ችሎታቸው

በሥነ ጽሑፍ ዝንባሌና አቋሙ በዓለም የታወቀው ደራሲው ሰርቫንተስ "ብዕር የአእምሮ ምላስ ነው" በማለት ለድርሰትና ለሥነ ጽሑፍ ተግባር ከፍተኛ ግምገማ እንደሰጠው ሁሉ በብሉያትና በሐዲሳት በመላለትም ቅዱሳት መጻሕፍት የምሥጢር ባህር ይዋኙ የነበሩት አባ ጊዮርጊስ ሥነ ጽሑፍ የአእምሮ ምላስ መሆኑን በመመዘን በተለያዩ የውጭ አገር ጸሐፊዎች እንደተገለጸው ሁሉ እርባ የሚሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ደርሰዋል ።

እነዚህም እስከ ዓርባ ቁጥር የሚደርሱት መጻሕፍቶቻቸው ለከፍተኛ ሊቅነታቸውና ቅዱ ንጽሕና ላለው ተግባራቸው ውጤታቸው ማረጋገጫዎች ፤ የሥራ ሰው ሰመሆናቸውም ታላቅ ማስረጃዎች ከመሆናቸውም በላይ ዕውቀታቸውን በጽሑፍ ያለገለጹትንና የጥያ ቅርሳቸውን በሥነ ጽሑፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያላስተላለፉትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ወቃሾችና ከሳሾች ናቸው ።

እንግዲህ ይህ እንዳይሆን የዛሬዎቹም ሆኑ የወደፊቶቹ ሊቃውንት ለተከታዩ ትውልድ ስለሚተላለፈው የሥነ ጽሑፍ ቅርስ ሊነቁበትና ሊጠነቀቁበት ይገባል የሚል መልእክት በዚህ አጋጣሚ ተላልፎላቸዋል ።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ከደረሷቸውም መጻሕፍት መካከል 1. አርጋኖን 2. ኖኅተ ብርሃን 3. ውዳሴ መስቀል 4. በ12ቱ ሰዓተ መዓልትና በ12ቱ ሰዓተ ሌሊት በዜማና በንባብ የሚደረስ መጽሐፈ ብርሃን (ሰዓታት) 5. የቤተ ክርስቲያን ፤ የሥላሴ የእመቤታችን የመላእክት የጻድቃን የሰማዕታት የነቢያትና የሐዋርያት ሰላምታ 6. ጸሎተ ፈትቶ 7. መጽሐፈ ምሥጢር ይገኙባቸዋል ።

ከነዚህም ጋር የቅዱስ ያሬድን ዜማ ስራቸው አጠናቅቀው ተምረው ለሌላው የሚያስተምሩ እንደመሆናቸው ለዜማው አገባብና አደራረስ ልዩ ልዩ ዓቅድና ሥነ ሥርዓት በመስጠት እጅግ አድርገው የደከሙና ያሰባሰቡትን በሥራ የገለጹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለውለታ ናቸው "ሰው ይሞታል ታሪክ ግን አይሞትም" የተባለውም ባህላዊ አነጋገር በቀጥታ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ይመለከታል ለማለት ያስችላል ።

### የደረሷቸው መጻሕፍት ከሆኑት ፍሬ ነገር በጥቂቱ

አርጋኖን መሰንቆ ወይም ዕንዚራ ማለትን ውና በአጠቃላይ የልዩ ልዩ ምስጋና መግለጫ ስልት ነው ፤ እንዲሁም ኖኅተ ብርሃን የተባለው እመቤታችን የብርሃን ደጃፍ ወይም የብርሃን መውጫ መሆንዋን በማስመልከት የተሰጠ ስያሜ ነው በመሆኑ ሁሉ ቱም መጻሕፍት እመቤታችን አምላክን ለ

ወደ ፲፰ ገጽ ዞሯል

# ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፰ የዞረ

መውለድ መመረጥዋን ፣ ንጽሕናዋን ቅድስናዋን ርኅራኄዋን ለሰው ልጆች ያደረገችውንና የምታደርገውን በጐ ተግባር ፣ እንዲሁም የአምላክን ሦስትንትና አንድነት የመሳሰሉትን የሚያመለክቱ ናቸው ።

ከዚህም ጋር ሰው ካልሠራ በሥጋውም ሆነ በነፍሱ የ ማይጠቀም መሆኑን የሚያረጋግጡ ተግባራውያን መፈክሮች መሆናቸው ታውቋል ። መጽሐፈ ምሥጢርም በዓለም ያለውን የሃይማኖት ልዩነት በዝርዝር የሚያስረዳ በመሆኑ ከፍተኛ ውጤት ያለው ነው ።

በአንድ ዓመት ውስጥ በሚገኙት ሦስት መቶ ስድሣ አምስቱ ዕለታት መጠን ስንክሳርን በመከተልና በዓላቱን በማስመልከት የደረሱት እግዚአብሔር ንግሥ የድርሰት ሰው መሆናቸውን አጉልቶ ያሳያል ።

አባ ጊዮርጊስን የሚያስመሰግናቸው የታሪክና የሥራ ሰው የሚያደርጋቸው ከትምህርት ሊቅነታቸው ጋር የድርሰት ሰው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሥነ ጽሑፋቸው በጥራቱ ፣ በምጥቀቱና በጥልቀቱ ሲለካ ሚዛናዊ በመሆኑም ጭምር ነው ።

## አባ ጊዮርጊስ ሁለተኛው ያሬድ ናቸው

የቅዱሳት መጻሕፍት ምርምርና የድርሰት ቅንብር ሙያ ከዜማ ስልት ችሎታ ጋር ተስማምቶ የተሰጣቸው አባ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ደቀ መዛሙርት ከአስተማሪዎቻቸው ከአባ ጌራ ዘጎድ ወሎ ሐይቅ አጠገብ ከሚገኘውና ደብረ እግዚአብሔር ከሚባለው ቦታ ፀዋትወ ዜማን በሙሉ ተምረዋል በበኩላቸውም ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት አስተምረዋል ።

ከዜማ ደቀ መዛሙርቶቻቸውም መካከል ልሳነ ዕፍረት መራሂ ዘቤተ ልሔም የተባለው ስመ ጥሩ ሊቅ ይገኝበታል ።

አባ ጊዮርጊስ በዜማ ማስተማር ብቻ ሳይወሰኑ እንደ ደቀ መዛሙርቱ ፍላጐት በአጠቃላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያስተምሩ እንደነበረ ይነገርላቸዋል ።

## የዕረፍታቸው ዜና

ሞት ፣ ታታሪ ሠራተኛም ሰነፍም የሚጓዝበት ጥርጊያ መንገድ ስለሆነ ብዙዎቹ ሊቃውንት በመቶና ከዚያም በላይ ባለው ዕድሜያቸው ሊሠሩ ያልቻሉትን ልዩ ልዩ ታሪካዊና መንፈሳዊ ተግባር በ60 ዘመን ዕድሜያቸው ብቻ አከናውነው ሐምሌ 7/1417 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የልደትና የሞት ቀናቸው አንድ በመሆኑ ይህንን የሚያነቡ ሁሉ ምን ያህል ይደነቁ ይሆን?

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ